# ማዕዘን

ወርሃዊ የድረ ገጽ መጽሄት ቅጽ 1



## እኔ ውሸቴን ነው

አንዳንድ ሰው በማያገባው ገብቶ ማንቦጫረቅ ይወዳል።

## የነፍሴ ውሀ ጥም

ዘመን ተሻጋሪ የሱዳን ሙዚቀኛ እንዳቀነቀነው. . .

# ዕውነትና ሁነት . . .

ዕውነት ነጻ ነው። ለዚህም ነው ከዕውነት ጎን መቆም እንጂ ዕውነትን ራሱን መሆን ማይቻለው።

ማዕዘን

MAEZEN.ORG

ማዕዘን

MAEZEN.ORG

## መልዕክተ ማዕዘን

ከተለያዩ አስጨናቂና ስለታማ የዕለት ተዕለት ክንዋኔዎች በመለስ የተጨነቀና የተረበሸ አዕምሮን ለማሳረፍ ወደሚቀርበን ጥግ ስንወጣ የምናገኘው ማረፊያ ነው። ማዕዘን ከተለያዩ የዓለም ውጥንቅጦች መልካሙን፣ በጎ ዕይታውን እንጎናጸፍና እናመሰግን ዘንድ፣ እናርፍ ዘንድ በሎም የዓለምን ውበት እናደንቅ ዘንድ የተበረከተልን ነው። ማዕዘን ለሁሉም ከሁሉም ቦታዎች የተመጠኑ እና የተመረጡ የጥበብ ስራዎችን፣ ሁነቶችንም፣ ታሪኮችን፣ ጥቅሶችን በመተንተንና ልዩ ቀለም በምስጠት ለተደራሲው ያቀርባል። ከተደራሲውም ለዩ መልዕክትና ዕየታዎችን ያስተናግዳል። ይህ ማዕዘን አገራችን ኢትዮጵያ ካላት በጎ፣ እጅግ ማራኪና ቅይጥ ባህል ከሰሜኑም፣ ከደቡቡም፣ ከምስራቁም፣ ከምዕራቡም ምንጭ በመቅዳት ካንዱ ዋንጫ ወዳንዱ ዋንጫ በማዛወር፣ የተለየ ቃናን የተለየ አቅጣጫን ለማሳየት የሚተጋ የእይታ ማዕዘን ነው። እናም ወደዚህ ማዕዘን የምትመጣ/ የምትመጪ ከሆነ በዚህ በኩል የሚታየው ውበት፣ ጥበብና ተረክ ሰርክ ዓዲስ ይሆን ዘንድ የራስን ጣዕምና ማንነት እንደ ስጦታ የሚበረከትበት ቦታ ነውና ራሥሽን/ ራሥህን እንዳትረሺ/ እንዳትረሳ።

maezen.org

Arts Destination



# ዕውነትና ሁነት



ዕውነትን ከሁነት የሚለየው ነገር ልክ የጥሬ ዕቃ እና የምርት ውጤት ዓይነት ነው። አንድን ሁነት በምናባችን እና በአዕምሮአዊ አመክኒዮዎቻችን አሳልፈን ከአካባቢያችንና ከ ባህላችን አንጻር እናሸገውና የራሳችንን ዕውነታ እንፈጥራለን። ስለዚህ እኛ ዕውነት የምንለው የሁነት ተረፈ ምርትን ነው እንጂ ዕውነትን አይደለም። እውነት በተቃራኒው ከኛ አመክንዮም፣ ምናብም፣ ባህል ፣ ዘይቤም የጸዳ ነው። ዕውነት ነጻ ነው። ለዚህም ነው ከዕውነት ጎን መቆም እንጂ ዕውነትን ራሱን መሆን ማይቻለው። እናም ጥበበኛ በሁነትና በዕውነት መካከል ያለውን ልዩነት ተገንዝቦ ሁሉም ሰው ለራሱ ዕውነት ነው ብሎ ያመነውን የሁነት ተረፈ ምርት ወይም የሁነት ውጤት የተለያየ መልክ በመስጠት ኩሎ እና አሳምሮ ወደ ዓለም መድረክ ያቀርበዋል። የማንም ዕውነት ለማንም ግልጽ ላይሆን ይችላል፤ ማንም ስለማንም ዕውነት ላይገደው ይችል ይሆናል። ነገር ግን የጥበብ ሰው የሁሉንም ዕውነት ያስውባል። ልክ ግንበኛ ገንብቶ እንደሚኖረው ሁሉ ጥበበኛም  ዕውነታን በማስዋብ ይኖራል። ሰዎችንም ዕውነታቸውን እንዳይሸሹትና ከዓለም እንዳይቆራረጡ ውበትን ይገልጥላቸዋል።

# ሀጫሉ፡ መኖር ወይስ አለመኖር?



ሀጫሉ ሁንዴሳ ቦንሳ በሙዚቃው ውስጥ በማህበረሰብ ውስጥ የኖረን ቁስል በነዛሪ ድምፁ ያሰረ አስሮም ጠፋፍ ያደረገ ቄሮ ከአንደበቱ ኩልል በሚሉት ቃላት በህይወቱ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በማህበረሰብ ውስጥ ያለን ህመም ታሞ ያስታመመ ፣ አስታሞ ኖሮ ያልጠገበውን ህይወት ገብሮ ከብዙ ከንቱዎች ቀድሞ የተሸኘ ቄሮ...

"ምኑን ኖርኩት" ሲል በደመፀው ሙዚቃ ታሪክን ከህይወት አሰናስሎ... ሥነ—ሡብን በአንድ የፍቅር ረሀብ ውስጥ ደልድሎ በጉሮሮው ስሎ በጥበብ ወዳጆች ላይ ያንቆረው የመለያየት ህመም... በመሰረቱ ወዳጅ ከወዳጁ፣ ቤተሰብ ከዘመዱ፣ እህት ከወንድሙ፣ ጓደኛ ከጓደኛው፣ በአጠቃላይ ፍቅር የተበተነበትን ሁነት እየጠቀሰ ይቆዝማል ይህ ጥበበኛ ቄሮ ያፈቀራትን ቀሬ በወደቀበት የጥቅመኞች ግርዶ ምክንያት ናፍቆ ማጣቱን፣ ለፍቶ መገታቱን ፣ ካፈቀሩት የመለያየት የሚያመጣውን ማቄምና የሚወልደውን የማይቆም፣ ደርሶ የማግኘት ፍላጎት ያልተረዱት እነርሱ የለያዩን ቢሆንም እኛ ግን አይገባንም። ሲል ያዝናል በስንኞቹ የመገፋትንና ራስ ወዳድ ባለጊዜዎች በፍቅር ህይወቱ ላይ የጣሉበትን ጠባሳ ያቀነቅናል። ጥቅም ሲሆን ባህል፣ እሴት፣ እንደ ፍቅር ያሉ ከተራራ የከበዱ የሰውነት መርሆዎች ሳይቀሩ እንደሚገፉና በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሰው እንዴት ኖርኩኝ ሊል ይቻለዋል ሲል በተጠይቅ መንፈስ ውስጥ አድማጩን ይዞት እልም ይላል፤"Diiganii gaara sanaa,
Gaara diigamuu hin-mallee,
Nu baasaan addaan baanee, nuu
addaan bayuu hin-mallee."
አፍርሰው ያን ተራራ ፥ ማይገፋውን ነቅንቀው ·ፀኛ·መሀል·ግርዶ·አኖሩ ፥ ·ከፍቅራችን ጦም አውለው · ·ሆብታም ሆነን ድጁ·ሞልቶ፥ ·የራበንን·ፍቅር ነጥቀው · ለያዩን ሳናስበው ፥ የውሸት ሳቅ አሳስቀው የሚል የመስላል . . . በዚህ የቁጭት ዜማ ውስጥ በሚሞዝቀው "ኖስታልጂክ" ወይም ደግሞ የቆየ እና የተቀበረ ስሜትን ፈንቃይ የሆነና በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ያለውን የጠለቀ የባህል ትሥሥር በምናብ ቦታው ላይ ወስዶ የሚጥል ነበር፤ በዚህ ዜማ ውስጥ

# አልሰማ ቢል ልቤ...

ቴዎድሮስ ካሳሁን መጨረሻ ላይ ካሳተመው አልበም ውስጥ የአድማጭን ቀልብ ከገዙ የፍቅር ዘፈኖች መካከል ‘ያምራል’ አንዱ ነበር። የ ‘ያምራል’ን የሙዚቃ ውበትና ትርጉም ከሞዛቂው በላይ ለማወቅ መንደርደር የምጣዱ ሳለ የእንቅቡ ተንጣጣ ይሆናል። ከአድማጮች አንዱ ከቆመበት ማዕዘን የዘማውን ፍሰትና የግጥሙን ስሜት እንደሚከተለው አይቶታል... አንድ በፍቅር የተጨነቀና የተቃጠለ የውበት ሽኑፍ ያለበትን የሀሴት ስቃይ ... ከጥበት፣ ከራስ በመነጠል፣ እና ራስን ከመርሳት ብሎም ከቁጥጥር ውጭ መሆንን አያይዞ ይገልፀዋል...“ስፍራ ጠበበው ያንቺ ውበት ፈክቶ ሲታይ...ደምቆ እንደ ፀሀይ” በዚህ ስንኝ የተፈቃሪዋ ውበት የርሱን ከባቢ እንደሞላው ስሞታ በማቅረብ ይጀምራል። ስሞታው ቀላል አይደለም፤ ሰው እንኳን የፀሀይ ብርሀን ላምባም በቀጥታ ካይኑ ሲገጥም ይቃጠላል። እናም በዚህ ስንኝ የትም ቢሄድ የማያመልጠውና የማይጠለልበት የውበት ፍካት ገጥሞት “ናና እየኝ” እያለ ውስጠ ልቦናውን ያስገብረው ይዟል። እናም በቃ እጅ ሰጥቷል ምርኮኛም ነው። ታዲያ ይህን ስንኝ ዜማ ሲሰጠው ሙሾ እንደሚያወርዱ ሁሉ ዋይ ዋይ ያስብላል። “ያምራል ያምራል... ... ያምራለ” በቃ ሙሾ ነው። ለውበት እጅ የሰጠ አፍቃሪ በዚህ “ዜማ ዋይ ዋይ” ከማለት ውጪ ሌላ አማራጭ አይተውለትም።ደግሞ በጣም የሚገርመው ቀልቡን እንዲህ ያስረገደውን ውበት የሳለባቸው ቃላት ሁሉ የተፈጥሮ አካላት ናቸው። ውበቱ እርሱ ስላፈቀራት የጎላ እንጂ ከሌላው ሰው የገነነ ተፈጥሮ ስላላት አይደለም። ይህንንም ቅንድብ— በኩል ሲለበጥ የሚሰጠውን ጥቁረት አንስቶ ይጀምርን እንደ ገና ፅድ ላለም መሞሸርን እስከመለፈፍ ይገፋዋል። ከዚህም ባለፈ ውቧ ሶሪት ወፍ ያሸበረቀቸረበትን ላባ ይመዛል። በሶሪት ውብ ወፍ ነች። ላባዋ ግን ይገልጣታል። ልክ የአንበሳ ጎፈሩ፣ የፅጌረዳ ዕንቡጡ የሸማ ጥበቡ እንደሚታየው ሁሉ የሶሪትም ላባዋ ይጎላል። ሩቢም እንደዛው ነው። ሹም ሲጀምር ከሁሉ የላቀ ክብር አለው፤ በአሁኑ ወቅት አንድ ሹም ኒሻን እንደሚያደርገው ሁሉ የድሮ የምስራቅ ነገስታት... ከዘውዳቸው ላይ ሩቢ ያስቀምጡ ነበር። ከወርቅም ከአልማዝም ከዕንቁም የጎላ ጌጥ ! እናም በዚህ ሁሉ ፍካት ውስጥ ይ ምርኮኛ ማምለጫ አላገኘም። በግራም በቀኝም በኋላም በፊትም መሄጃ የለውም።ታዲያ ይህን ሲያውቅ ተንበርክኮ መሬቱን እየቧጠጠ ደረቱን እየደቃ ሙሾውን ያወረደ ይመስላል።“ያምራል ያምራል ዋይ ዋይ !” “አልሰማ ቢል ልቤ...”በፍቅር የተነካ ሰው ይህ ደካማ አፍቃሪ ከልቡ ጋር እንኳን ድርድር መቀመጥ አልቻለም። ይከንፋል ይሄድበታል። ለነገሩ ውበት ሲጠራ ማን ሌላን ያዳምጣል?? ለውበት መታዘዝ የሰውልጅ ንጥቀታዊ ምላሽ ነው። የአመክንዮን መልካም ፈቃድ አይጠብቅም። ልብ ለውበትና ለጥበብ እጅ ይሰጣል። በየሄደበት ሁሉ ውበት ካለ ከሌላው የህይወት ሂደቱ ሁሉ መነጠሉ አይቀሬ ነው።በዛብህን ከደብሩ፣ መጅኑንን ከአቅሉ፣ ሮሚዮን ከህይወቱ የነጠለው። ውበት የት እንደሚጥል አይታወቅምና በዚህ ዜማ ከማንነት የተነጠለ ስብዕናን ይሰብካል።





## ጥበብ እና ኪን



ኪን የጥበብ ቅርንጫፍ እንጂ ራሱ ጥበብ አይደለም። ከላይ በሰፊው እንደዳሰስነው ጥበብ የዕውነታን ትርጉም ፈላጊና ዕውነትን ባለበት ሁሉ የሚኖር በቋንቋና በዕውነት መካከል ያለውን የተግባቦት መስመር የሚያሟላ ሲሆን ኪን ደግሞ ጥበብን ወደ መድረክ የሚያወጣው የሚያቀርበው ነው። ጥበብ ፍለጋ ሲሆን ኪን ያገኘውን ትርጉም ወደ ህዝብ ማስተላልፊያ መንገድ ነው። ኪን በጥበብ ጥላ ስር ካልሆነ መለኪያ የለውም። ውበቱም፣ ልኬቱም የሚታወቀው ከጥበብ እና ከ ዕውነት አንጻር ሲቃኝ ነው፣። እናም ማዕዘን ጥበብን ከተለያዩ አቅጣጫዎች ትፈልጋለች። ያገኘችውንም ለአንባቢያን ታቀርባለች።

## ኢትዮጵያ በፎቶ











ሃጫሉ:... ፍቅር ዋና ነጥቡ ይሁን እንጂ የማህበረሰብ እሴት መበተንን ክለብ በመነጨ የሀዘን ስሜት ይገልጠዋል። በመሰረቱ በስንኞቹ ውስጥ በሃይል ከመገፋት ይልቅ መሰሪዎች አታለውና አሳስቀው በአድር ባይነት የፈጠሩት የጥቅም ሰንሰለት የኦሮሞን ህዝብ እሴት ንደውታል ነው መልዕክቱ። ታዲያ በዛ ውስጥ ፍቅሩን ማጣቱ ያንገበገበው ወጣት መቼ ይሆን የማይሽ እያለ . . . መለያየቱ የናፍቆቱን ነበልባል ይብልጥ እንዳቀጣጠለውና እንደውም ካለርሷ ኑሮ ምኑን ኑሮ ሆነ እያለ ብውስጡ ያነባውን እንባ በዜማ ያቀነቅነዋል. . . ወደ መጨረሻው አካባቢ በህይወቱ የገጠመውን ባጶነት የገለጸው እንዲህ ሲል ነበር. . . “የሌሊት ወፍ ማታ ትላለች ጭው ጭው ላዋቂ ምስክር ጠባሳ እንኳ ሳይተው የናፍቆትሽ ጠኔ ደ’ ስታዬን ላጨው ታዲያ ምኑን ኖርኩት ካንቺ ተለይቼ  በላኝ ሀሩር ቁሩ ራቁቴን ቀርቼ የሩቅ ሀገር ተስፋ መች እንቅልፍ ይሰጣል የፍቅርሽ ህመሙ ሰባብሮ ይጥላል”  እያለ ያነባባቸው ስንኞች በተለይ የቁስሉን ደረጃ ባይነ ህሊናችን እየሳልን አብረን እንድንታመም፣ ከሀዘኑ ጋር አብረን እንድናዝን ያደርገናል። ታዲያ ይህ ቁሮ በዚህ ደረጃ የማህበረሰብን ስሜት ሰቅዞ በመያዝ በታሪኩ ውስጥ በልማት ስም የተፈጸመን በደል በእያንዳንዱ ቤት ምን መልክ እንደያዘ ያሳየበት ታላቅ የትግል ዜማ ተደርጎ እንዲወሰድ ምክንያት ሆናል። ለዚህም ይመስላል በኦሮሞው ብቻ ሳይሆን በመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሳይጠገብ መሄዱ ለዜጋው ሁሉ እጅግ አስደንጋጭና አሳዛኝ ሆኖ ማለፍ የወጣቱ ድምጻዊን በጥልነትና·ተወዳጅነት በድማቅ ጽፎታል።··



ማዕዘን
MAEZEN.ORG



# የጥበብ መፍለቂያ

" ዕውነት አስቀያሚ ነው፤ የጥበብ አስፈላጊነትም ከእውነታ እንዳንሸሽ ማድረጉ ነው።" ይህ የዕውቁ ጀርመናዊ ፈላስፋ ፍሬድሪክ ኒቼ ንግግር ነው። ይህ ጥቅስ ከተለያዩ ማዕዘኖች ሊቃኝ ይችላል። ከማዕዘኖቹ ባንዱ በኩል ስናየው ጥበብ ለህይወት ለዛ የመስጠትን ሚና እንደሚጫወት ያሳየናል። ዓለም ዘላቂነት በሌላቸው ሁነቶች መሞላቷ በራሱ አስቀያሚ ያደርጋታል። በምድር ላይ የምንም ነገር ቋሚ ባለቤት መሆን አለመቻል የያዝነውን እንዳናጣጥምና ባለን እንዳንደሰት እንቅፋት ይሆኑብናል። በዚህም ምክንያት ከሰው ልጆች ከፊሉ አልጠግብ ባይ ይሆንና ሰው የያዘው ሁሉ ያምረዋል። ይህም ስግብግብ ያደርገዋል። ከፊሉ ደግሞ ባለው ነገርም አይደሰትም፣ የሰውንም አይመኝም ባይሆን ሁል ጊዜ ያማርራል፤ ያለቃቅሳል፣ ይተቻል። ነገር ሁኔታውን ለመቀየር አይሰራም፤ አይደክምም። እንዲህ ዓይነቱ ደግሞ ሰነፍ ነው። ሌላኛው የሰው ክፍል ደግሞ እይታዎችን ይፈጥራል። ነገራቶች ከዕውነታቸው ይልቅ ትርጉማቸው ምን እንደሆነ ለማወቅ ይጥራል። ሁነቶች በበጎም ሆነ በመጥፎ አኳኋን ቢመጡም አመጣጣቸው ሳይሆን መንሳኤያቸው፣ የመጡበት አቅጣጫ እና በመምጣታቸው የሚከሰተውን ውጤት ይፈልጋል። ከያንዳንዱ ሁነት ቀዳሚና ተከታይ እንደሚኖረው በመረዳት ምናብ ሰጥሞ ከዕውነታው ይልቅ ዕውነታው የመጣበትን መንገድ ይከተላል፣ የስነ ፍጥረትን እምቅ ትርጓሜ ፍለጋ ይወጣል። ይህም ጠቢብ ያደርገዋል። ጥበብ መነካትን ይፈልጋል። ጥበብ መጥለቅን፣ መጥፋትን፣ ፍለጋ መውጣትን ይሻል። ጥበብን ለማግኘት በመጀመሪያ ከልብ የመነጨ ማጣትን መኖር አለበት። ያላጣ ቢያገኝም ያገኘውን ጸጋ የማወቅ ዕደሉ የጠበበ ነው። ጥበብ ከጠባብና እጅግ ውስን በሆነው ምድር ውስጥ ሰፊና ወሰን የለሽ ትርጉምን ማግኘት ነው።የጥበብ ምንጭን ለመረዳት አንድሰው የጎደለውን ማወቅ አለበት፤ የጎደለውን ማያውቅ አሊያ ደግሞ ካለበት አሳልፎ የማይመለከት፣ የማወቅ ረሀብ የሌለበት ሰው ፍለጋ አይወጣም። ስለዚህ ጥበበኛ ጉዳዩ እውነተኛ ለመሆን ሳይሆን ከዕውነት ጎን ለመቆም ነው። ዕውነት ወደመራው ለመሄድና ዕውነት ወደታየበት ልማቅናት ሁሌም ዝግጁ ነው። ምክንያቱም ዕውነት ምን ጊዜም ክሁነት ተነጥሎ የቆመ እንደሆነ ያውቃል።



# የነፍሴ ውሀ ጥም

አብዛኛውን ኢትዮጵያዊ ከሱዳን ሙዚቃ ጋር ያስተዋወቀው ሙሀመድ ወርዲ ከዘፈናቸው ዘመን አይሽሬ የፍቅር ዜማዎች መካከል "ቲስዓት ዓሸር ሰና" አንዱ ነው። ኢትዮጵያውያን በተለምዶ "ሰበርታ" ብለን የምንጠራው ማለት ነው። ዓረብኛ ቋንቋን በመጠኑም ቢሆን ለሚረዳ ሰው እጅግ ግልፅና ልብን ሰርስሮ የሚገባ ዓረብኛ ቋንቋን በመጠኑም ቢሆን ለሚረዳ ሰው እጅግ ግልፅና ሰርስሮ የሚገባ የቃላት አሰዳደር ያለው ዜማ ነው ነው። የስንኞቹ አንጓ ቃላቶች... ጥማት፣ ናፍቆት፣ ፍቅር፣ ጥፍጥና፣ ቃጠሎ፣ ትዕግስት ምኞት እና ይቅርታ ሲሆኑ በቃላቶቹ እየተጫወተ የፈጠረው የልመናም አንጀት የመብላትም ገፅታዎች በማሳየት በአድማጩ ልብ ውስጥ የሀውነተኛ ፍቅርን ስሜት ይጭራል። · · · · "ሰበርቱ ወስተነይቱ" ... ታግሼ ጠብቅኩሽ በማለት ይጀምራል። ስላንቺና ስለኔ ብዙ ብዙ የምመኝ ብሆንም ነገር ግን አፍቃሪ በመሆን መወትወት አልችልም። መወትወት ማስገደድና መጎተት የዕውነተኛ ፍቅር መገለጫዎች አይደሉምና ብዙ ብፈልግሽም በእጅጉ ብመኝሽም አፍቃሪነኝና ከመጠበቅ ውጪ አማራጭ የለኝም ይላል... ልቤንም እንዲህስ ስል ላስታግሰው እንጂ... ከመጠበቅ ውጪ አማራጭ የለኝም... ነገ በገነት እስካገኝሽ አረጋጓለሁ። ካንቺ ጋር የዝንት ዓለም ደስታን እመኛለሁ። ከአንቺ ጋር ጣፋጭ ህይወትን ማሳለፍ የዘውትር ምኞቴ ነው። ህልሜ ነሽ ይላታል ለፍቅሩ... 'ዓጠሽቲ ቀልቢ' ይህ እጅግ ማራኪ የሆነ ገለፃ አረብኛውን በቀጥታ ብንተረጉመው 'ልቤን ጠማሽው' የልቤ ጥማት ነሽ... ውስጤ ያንቺን የፍቅር ውሀ ካልተጎነጨ አይትፍም የሚል



ይመስለል። 'ጥማት'ን በገለፀበት ስንኝ ውስጥ ' "ሳይሽ ሰርክ ይደንቀኛል ውበትሽ ይደምቅብኛል ነይና 'ባክሽ አድኚኝ አትለይ ፍቅርሽ ጠምቶኛል" የሚል ዓይነት ውርስ ትርጉም ያለው የልመና ድምፀት ያሰማል። የፍቅርን ስቃይ ከክፋት ስቃይ የሚለየው ፈልገው የሚሰቃዩት በመሆኑ ይመስላል። ፍቅር ውበትን በሀይለ ቁጥር እያሳደገ በልብ ውስጥ አንዳች ቦታን ሳያስተርፍ በተፈቃሪው ጉዳይና ጉዳይ መጠመድን ይሻል። ይህ ታዲያ በራስ ላይ የማይበርድ እና ትንግርታዊ የሆነ የስቃይ እሳትን መጫር ነው። በፍቅር መቃጠል አሜን ብለው ከተቀበሉት በኋላ የሚከፍሉትን ማናቸውንም መስዋትነት ሲከፍሉ በደስታ ነው። ሲሰቃዩ በደስታ ነው። ብቸኛ ፍላጎታቸውም ይህን ስቃይ ተፈቃሪው ለርሱ ብሎ የተደረገ መሆኑን ያውቅላቸው ዘንድ ነው። እናም በዚህ ዕፁብ ድንቅ ግጥም ውስጥ ያፈቀራትን ሴት ሰርክ ትዋቢብኛለሽ እንደውም ሁል ጊዜም ዕንቡጥ በሆነው የዕድሜ ክልልሽ እንዳለሽ ሁሉ የ19 ዓመት ኮረዳ መስለሽ ነው ምትታዪኝ። 19 ዓመት በተለይ በመካከለኛው ምሰራቅ ባህል የሴት ልጅ ውበት የሚጎመራበት እና የሚሰረግት እንደሆነ ይታመናል። ዕውነታውም ለዚህ እጅግ የቀረበ ነው። ዘፋኙም ይህንኑ በመንተራስ አንቺ ለኔ ሰርክ ትዋቢያለሽ ልክ እንደ 19 ዓመት ኮረዳ የፅጌረዳ ውበት፣ አንፀባራቂ ውበት ያየ ሁሉ በግርምት ቆሞ የሚደነቅበት ዓይነት የማይጠገብ ውበት ነው ያለሽ። ለዚህም የልቤ ንግስት እንደሆንሽ ትቀሪያለሽና እባክሽ ጠምተሽኛል። እስካሁን በትዕግስት ጠብቂያለሁና ድረሽልኝ። አትፈሪኝ አትራቂኝ እያለ ዜማውን ይዘጋዋል...

MAEZEN.ORG

# እኔ ውሸቴን ነው



አየሰው ነገር ከባድ ነው። አንዳንድ ሰውማ ጭራሽ በማያገባው ገብቶ ማንቦጫረቅ ይወዳል።በፍቅር ዓለም ደግሞ እንዲህ ያለውን ወይም እንዲህ ያለችዋን ለፍቅር ተብሎ አይመረጥምና አንዳንድ ጊዜ ካለንበት የኑሮ ዘይቤ አሽቀንጥሮ ይወረውረናል። እጅግ ወደማናውቀው ዓለምም ይከተናል። አርቲስት ምኒሊክ ወስናቸውም እንዲህ ባለው ወህኒ ተወርውሮ ከማያውቀው ዓለም ለመውጣት እየተፍጨረጨረ ሳለ በዙሪያው ያሉ ወረኞች ስለ ፍቅሩ ይጠይቁታል... ያላወቀውን፣ ያልገባውን፣ ያላጣጣመውን የፍቅር ዱብዳ እንዴት ይግለጠው? እንዴትስ ይናገረው? ወረኞችም አልተዉት፣ እርሱም በውል አልተገለጠለት... በፍቅራችን መሐል...
ጥያቄው በዝቶብኝ
እኔ ውሸቴን ነው
አልወዳትም ያልኩኝ
ብሎ ይጀምራልአዲስ ፍቅር እኮ ያሳፍራል፤ እንደውም ግራ ያጋባል። አንዳንዴ አፍቃሪው የሚያሳየው ባህሪይ ለተፈቃሪው እና ለተመልካች ግራ ይሆናል። አይቶ መደበቅ፣ በሰፈራቸው ያለ ጉዳይ መመላለስ፣ ያው ተፈቃሪው ሲመጣ ባላየ ማለፍ... ፍቅር ከመግለጥ ይልቅ ካድ አድርጎ በህመሙ መማቀቅ የሚመርጥ ሞልቷል። ይሁንና አንዳንዱ እንደ ጋሽ ምኒሊክ ህመሙን መቋቋም ይከብደውና "እኔ ውሸቴን ነው" ሲል በዜማው ፀፀት እንደበላው ይናገራል። ፍቅር ግትር ያደርጋል፤ እልኽ ውስጥ ይከትና፣ ሳትነግረኝ ወይም ሳይነግረኝ በሚል አሽቅድምድም አጓጉል ርምጃዎች ያስወስዳል። ይህንን ሲወቅስ አንዱ አፍቃሪ እንዲህ ሲል ተሰኝቷል...
"ትመጣለች ብዬ መሄዱን ብተወው
ተሞሽራ ሄደች ፍቅሯን በሆድ ይዛው"
ታዲያ እንዲህ ያለውን ያልተገባ እፍረትና ያለቦታው የሆነ ኩራት ፍቅርን እስከወዲያኛው ያሳጣቸውና... ኋላ ካለፈ ወዲህ የገፉት ፍቅር ፀፀትና ህመምን ትቶላቸው የሄዱ ብዙ ናቸው። ታዲያ በ"ውሸቴን ነው" ዜማ ውስጥ ልብ ውስጥ የተቀበረን ፍቅር በማንኛውም ሰው ግፊት እና ውትወታ መተዉ ህመም ሆኖ እንዳሰቃየው ይገልጣል ጋሽ ምኒሊክ። እንደውም
"ጠያቂው ቢያስጨንቀኝ
ስለፍቅርሽ ትዝታ
አልወዳትም አልኳቸው
እንዲያገኙ ደስታ" በሚለው ስንኝ ውስጥ እርሱ እርሷን እንዳይወዳት፣ በፍቅሯ እንዳይወድቅ የሚፈልጉ አካላት መኖራቸውን ይነግረናል... በነዚህ ስንኞች ውስጥ የማህበረሰቡን ባህል፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ ዘር፣ ሀይማኖት ሁሉ እያስገባን ልናየው የምንችለው ከባድ መልዕክት አለ። ምን አልባት እንዳይወዳት የፈለጉት የደሀ ልጅ ናትና አትመጥንህም ብለው የሚወተውቱ ቤተሰብ ይኖረው ይሆናል እናማ ጋሽ ምኒሊክ በዘፈኑ ከመፀፀቱ በፊት ያለውን የማህበራዊ የኑሮ ልዩነት ሳይመለከት፣ ፀወረኞች ግፊት ሳይወድቅ ፍቅሩን ቢገልጥና ቢቀበለው... እንዲህ ያለ ፀፀት ውስጥ ባልገባ ነበር። ማን ያውቃል... ምን አልባት አልጨከነችበት ይሆናል። ፀቱን አይታ፣ ልመናውን ሰምታ የምትመለስለት ሰው ይኖር ይሆናል... ሁለተኛ ዕድል የሚሰጠው ይኖር ይሆናል...ይሄኔ ያለበትን ፍቅር ረጋጭ የሆነ የባህል እና አጉል ዕምነት ሰንሰለተወ ሰባብሮ ይወጣል። የታሰረበት የፍቅር ሰንሰለትም ይሄኔ ወደ የፍቅሩ ጌጥ ይሆንለታል።... ምናልባትም አባትየው ዘሯ ከዘራችን አይገጥምም። ብለው ገፍተዋት ይሆናል። ምን አልባትም ጓደኞቹ አስቀያሚ ናት አታምርም ብለውት ይሆናል... Nገር ግን ፍቅር፣ ፍቅር አይፈርድም። ፍቅር እከሌ እንዲህ ነው እከሊት እንዲህ ናት አይልም። ይጥልሀል፤ ከዚያ ልክ ባህር ላይ እንዳለህ ሁሉ ወይ ተቀብለኽው ነፃ ሆነህ ሳትፈራ ትንፈላሰስበለህ፤ እርሱም ያንሳፍፍሀል።
አሊያ ደግሞ ትፈራዋለህ። ትጨነቃለህ። ከዚያም ሰውነትህ ይኮማተርና ለውሀው ትከብደዋለህ፤ ያሰጥምሀልም። እናማ ጋሽ ምኒሊክ በዘፈኑ ከመፀፀቱ በፊት ያለውን የማህበራዊ የኑሮ ልዩነት ሳይመለከት፣ ፀወረኞች ግፊት ሳይወድቅ ፍቅሩን ቢገልጥና ቢቀበለው... እንዲህ ያለ ፀፀት ውስጥ ባልገባ ነበር። ማን ያውቃል... ምን አልባት አልጨከነችበት ይሆናል።
ፀፀቱን አይታ፣ ልመናውን ሰምታ የምትመለስለት ሰው ይኖር ይሆናል... ሁለተኛ ዕድል የሚሰጠው ይኖር ይሆናል... ሄኔ ያለበትን ፍቅር ረጋጭ የሆነ የባህል እና አጉል ዕምነት ሰንሰለተወ ሰባብሮ ይወጣል። የታሰረበት የፍቅር ሰንሰለትም ይሄኔ ወደ የፍቅሩ ጌጥ ይሆንለታል።





# ከማህበራዊ ጸረገጽ የተመረጡ ልጥፎች

## እየተደማመጥን፤ (በዳምጠው)

## (በእውቀቱ ስዩም)

የሆነ ጊዜ ከሬድዮ ጣቢያዎቻችን እንዱን ሳዳምጥ ጋዜጠኛው፤"
" አድማጮቻችን እንዴት ዋላችሁ ፤ ሰላማችሁ ብዝት ይበል ፤ በዛሬው እለት የምንወያየው ካንገብጋቢ የማህበራዊ ችግሮቻችን ባንዱ ዙርያ ነው ፤ አንድ እንግዳ ስቱድዮ ድረስ ጋብዣለሁ ... እስቲ ስምዎትን ለአድማጮቻችን አስተዋውቁ" እንግዳው : " የመቶ አለቃ ገረመው እባላለሁ" " እሺ ሃምሳ አለቃ ገረመው ይቀጥሉ " " ባሁኑ ጊዜ ትልቁ አንግብጋቢ ችግር አመት በአል ጠብቆ ዋጋ መቆለል ነው፤ ነጋዴው ባዘቦት ቀን ሰላሳ ሺህ ብር የሚሸጠውን በሬ ፤ የገና በአል ሲቃረብ በትራክረት ዋጋ ይሸጥልናል፤ ይሄ በእውነት ነውር ስለሆነ መንግስት አንድ ነገር ቢያደርግ ጥሩ ነው ባይነኝ" ጋዜጠኛው - እንግዲህ ሻምበል ገረመው የሚሉትን ሰምተናል፤ ሻለቃው በድፍረት እንዳስቀመጡት ከሆነ፤ የአመት በአሎቻችን አለቅጥ መብዛት አገራችንን ለከፋ ድህነት ዳርጉዋታል ፤ መንግስት በአመት በአላት መብዛት የሚባክነውን ጊዜ ለመቀነስ ከአመቱ ቀናት አንዱን ቀን መርጦ የገናን ፋሲካንና የመውሊድን በአል ባንድ ላይ እንዲከበሩ ቢያደርግ ጠቃሚ ነው ባይ ናቸው ፤ እንደኔ አረዳድ ! በዚህ አነጋጋሪ ጉዳይ ላይ የአድማጮቻችን ምላሽ ምን ይሆን?" አንድ አድማጭ ገባ፤ " ሬድዮየን ገና አሁን ስለከፈትኩት የተናገራችሁትን አላዳመጥኩትም፤ ያም ሆኖ ስለ መቶ አለቃ ገረመው ጥቂት ለመናገር ያክል ፤በጣም አስቸጋሪ ሰው ናቸው፤ በጎረቤትነት አምስት አመት ቆይተናል፤ እድርም ነበረን፤ ተጨቃጫቂና ሰካራም መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ሶስት መቶ ብር ተበድረውኝ አልመለሱም ! ያኔ ሶስት መቶ ብር እንደዛሬው አልነበረም፤አንድ ሄክታር የከረንቦላ ጠረጴዛ ይገዛል"
" በተነሳው ሃሳብ ላይ ብናተኩር"
አለ ጋዜጠኛው አቋርጦ : :
" ኦኬ ፤ ሲጀመር ስለጃንሜዳ የተናገሩት ነገር በሙሉ አንድም እውነት የለውም፤ ታከለ ኡማ በቲማቲምና በጎመን ሳያጨማልቀው በፊት ጃንሜዳ በየትኛውም ዘመን የገበያ ቦታ ሆኖ አያውቅም፤ ካጤ ምኒልክ ዘመን ጀምሮ ጊዮጊስና ቡና የፈረስ ጉግስ የሚወዳደሩበት ቦታ ነበር፤ ለዚህ ደግሞ ከመቶ በላይ የፎቶ ማስረጃ አለኝ ! ባስፈለገ ጊዜ አወጣዋለሁ" " ይቅርታ አድማጫችን፤ ከርእሰ ጉዳያችን በጣም እንደራቁ ላስታውሰዎት ነው፤ ስለጃል መሮ አለኝ ያሉትን መረጃ በሙሉ ለሚመለከተው አካል መሰጠት ይችላሉ፤ እኛ ወደ ጀመርነው ውይይት እንመለሳለን፤ አድማጮቻችን ! ደውሉልልን"ፌስቡክ ላይ የሚደረግ ክርክር ባጭሩ መንፈሱ ከዚህ አይርቅም !

# ሽመልስ ሆይ ተመለስ!

## (አማን መዝሙር)

ሽመልስ አብዲሳ ለምን በየግዜው እንደሚሳሳት አይገባኝም። አሁን ደግሞ ፌደራሊዝሙን አሞግሶ ትልቅ ስህተት ፈፅሟል። ሽሜ እዚች ሐገር ላይኮ ጥሩ ኢትዮጵያዊ ለመሆን መጥፎ ኦሮሞ መሆን አለብህ። ያመንክበትን ሳይሆን ያመኑበትን ንገራቸው። ስለፌደራሊዝሙም አታንሳ። ይሄ ኦሮሞ ኦሮሞ ምትለውንም ነገር ተው። ብትችል ዝም ብለህ ወያኔንና ኦነግን ተሳደብ። ከዚያ ነገስታቱን በወሬህ መሃል ጣልቃ እያስገባህ አሞግስ። ብትችል የአፄ ልብነድንግልን ምስል ታቶ ተነቀስ። ለኢንተርቪው ስትወጣ ምንም እንኳ የኦሮሚያ ፕሬዘዳንት ብትሆንም በአማርኛ ለማውራት ሞክር። ከተቻለ ደግሞ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ጥለት ያለውን ነጠላ ጣል አርግ። መሃሉ ላይ መስቀል የጨበጠ አምበሳ ቢኖርበትማ ምርጥ ነበር። ሽሜ ሆይ ጥሩ ኢትዮጵያዊ ሁን። የኢትዮጵያዊነት ኮንሰፕት በደምብ እንዲገባህ ደግሞ አማርኛ ሙዚቃዎች አዳምጥ። በተለይ በቴዲ አፍሮ "በሰማዩ ላይ ቢታይ ቀለም የሷ ነው እንጂ ሌላ አይደለም" እያልክ ምንም እንኳ ሬምቦ ሰባት አይነት ቀለም ቢሆንም የኢትዮጵያ ባንዲራ ነው ብለህ ግግም በል። እንኳን "አዲስ አበባ የናት ያባቴ ርስት ነች" ማለት ቀርቶ አዲስ አበባ ተለጥጣ ወለጋ ብትገባም ዝም ጀዴ! የሪሶርስ ባለቤትነት፣ ህገመንግስቱ የሰጠህን የልዩ ጥቅም መብት ራሱ በፍፁም እንዳታነሳ። ሃይማኖትህ ምንም ይሁን ምን በፍጥነት ወደኦርቶዶክስነት ወደቀድሞ ወደአባቶችህ ርስት ተመለስና ሰንበት በተስኪያን ስትስም ፎቶ እየተነሳህ ፌስቡክ ላይ ለጥፍ። ሽሜኮ ምርጥ ኢትዮጵያዊ ሁንልን። ደጋግመህ ኢትዮጵያ አትፈርስም እያልክ መፎክር አሰማ። ፌደራሊዝም ምናምን ምትለውን ነገርም እርሳው። ፍፁም በቋንቋም በባህልም በስነልቦናም የማንለያይ አንድ አይነት ህዝቦች መሆናችንንም አትርሳ። ምንም እንኳ አባንግ ሜቶ እስካሁን ሰው ነኝ እያለ ሰው ለመሆኑ recognition ፍለጋ የሚንከራተትባት ሐገር ብትሆንም። አንድ ነን። ዛሬም ፒያሳ ያለ አባት ሴት ልጁን ለአኝዋክ ወንድ ጨክኖ የማይሰጥባት ሐገር ላይ ብንሆንም አንድ ነን። ምንም እንኳ በየአደባባዩ ኦሮሚኛ ቋንቋ የወፍ ቋንቋ ስለሆነ ለቅዳሴ አይበቃም እየተባለ የሚሰበክባት ሐገር ብትሆንም አንድ ነን። ምንም እንኳ ኦሮሞን ለደቂቃ የማትታገስ ቁስሉ ላይ ጨው የምትነሰንስ በሰበብ አስባቡ አንገቱን እንዲደፋና እንዲሳቀቅ የምትሰራ ሐገር ብትሆንም አንድ ነን። ምንም እንኳ 400 ጉምዝ በአንድ ለሊት ተገድሎ ሲቀበር ፀጥ ያለች ሐገር ብትሆንም አንድ ነን። ምንም እንኳ የኦሮሞ ጋዜጠኛን ፣ የኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቲ መሪን፣ የኦሮሞ ዘፋኝን ፣ የኦሮሞ ባለስልጣንን እየነጠለች ለማጥፋት የምትሰራ ሐገር ላይ ብንሆንም አንድ ነን። ምንም እንኳ ከአንድ ኦሮሞ ኢትዮጵያዊ ለመሆኑ ከመታወቂያው ውጪ ሌላ የባህሪ ማተማመኛ የምትጠብቅ ሐገር ብትሆንም አንድ ነን። ስለዚህ ሽሜ ምርጥ ኢትዮጵያዊ ሁን። አለበለዚያ እንደተለመደው በቅፅበት ኢትዮጵያዊነትህን ተነጥቀህ ማዳጋስካራዊ ትሆናለህ።

# ከኢትዮጵያ ጋዜጦች የተመረጡ ጽሁፎች




## <<ለሰው ልጆች ሰላም. . .>>

ሔኖክ ያሬድ (ለሪፖርተር ጋዜጣ እንደጻፈው)

ከ1980ዎቹ መባቻ ጀምሮ በሬዲዮም ሆነ በቴሌቪዥን ይሰማ፣ ይደመጥ የነበረ አሁንም ደግሞ ሞገድ አሳብሮ የሚሰማ የሚደመጥ አንድ ዜማ/ዘፈን አለ፡፡ <<ለሰው ልጆች ፍቅር ለሰው ልጆች ሰላም፣ለሰው ልጆች በዓለም ዙሪያ ሁሉ ሰላም ይሁን ምድሩ ሁሉ፡፡>>ታዋቂውና አንጋፋው ድምፃዊ መሐመድ አህመድ ያቀነቀነው ሌሎች ድምፃውያንም በኅብረ ዝማሬ ዓምና ያቀረቡት የሰላም ጥሪ፣ የሰላም ደወል ነው፡፡በየዐረፍተ ዘመኑ ስለኢትዮጵያ ሰላም ያልተዘመረበት ያልተገጠመበት፣ ያልተተወነበት ጊዜ የለም፡፡ ሁሉም በየቤተ እምነቱ፣ በየደጅ ሰላሙ ስለሰላም ጸልየዋል፣ ስለሰላም ዘምረዋል፣ ስለ ሰላም አልቅሰዋል፡፡ ይሁን እንጂ በየዐረፍተ ዘመኑ የሰላም ድምፅ እየራቀ፣ ሁከት እየሰፈነና፣ ጦር ንቅነቃ፣ ዘገር ውዝወዛ መንሰራፋቱ ሰውን ለጥፋት፣ ለስደት፣ ለጉዳት መዳረጉ አልቀረም፡፡ሰላምና ጽንሰ ሐሳቡበአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በተዘጋጀው <<መዝገበ ቃላት ሐዲስ>> የሰላምን ፍች ከሌሎች የምሥራቅ ሴማዊ ቋንቋ ቤተሰብ ስያሜ ጋር እያይዘው አቅርበውታል፡፡ ሰላም በሱርስት (የሶርያ ቋንቋ) ሽላም፣ በዕብራይስጥ (የእስራኤል ቋንቋ) ሻሎም፣ በዓረብ ሰላም እንደሚባል ትርጉሙም ፍፁም ጤናን፣ ዕረፍትን፣ ዕርቅን፣ ፍቅርን አንድነትን፣ ደኅንነትን፣ ተድላ ደስታን፣ ሰላምታን ያቀፈ ጽንሰ ሐሳብ ነው ይሉታል፡፡ ሰላም ሰው ሲገናኝ፣ ሲለያይ የሚለው፣ የሚናገረው ወይም የሚጥፈው የቡራኬ የምርቃት ቃል ነው ሲሉም ያክሉበታል፡፡የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባዔ <<የሰላም ግንባታ ማሠልጠኛ>> በተሰኘው ጥናታዊ መድበሉ ስለ ሰላም ምንነት እንደሚከተለው አብራርቷል፡፡<<ሰላም>> የሚለው የአማርኛ ቃል የተሸከመው ጽንሰ ሐሳብ ከጦርነትና ከአመፅ ነፃ መሆን ከሚለው የአንዳንድ መዛግብት ቃላት ውሱን ድንጋጌ የሰፋ ትርጉም ይዟል፡፡ <<ሰላም>> ለሰው ልጆች ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታና ከመለኮታዊ ዕድቅ ጋር የሚጣጣም ሰብዓዊ ዕቅድ ከመሆኑ በፊት በዋናነት የእግዚአብሔር የራሱ ዓይነተኛ ባህሪ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም <<እግዚአብሔር ሰላም ነው>> (መጽሐፈ መሳፍንት 6፡ 24) በማለት ማረጋገጫውን ሰጥቷል፡፡ <<በቅዱሳት መጻሕፍት ሰላም የሚለው መሠረታዊ ቃል የሚያመለክተው በሰዎች ሕይወት ውስጥ ተሟልቶ መገኘት የሚገባውን ደኅንነት፣ ምሉዕነት፣ ፍፁምነትና ዋስትናን በመሆኑ ቃሉ የያዘው ፍቺ ላቅ ያለ ሐሳብን ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ሰላም ማለት ሰዎች በግል ኑሯቸውም ሆነ በማኅበራዊ ግንኙነታቸው ወቅት ሊኖራቸው የሚገባ ሁለንተናዊና ምሉዕ የሆነ የሕይወት መገለጫ ነው ማለት ይቻላል፡፡<<ሰላም>> (Sala'am) የሚለው የዓረብኛው ቃልም እንዲሁ ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ጽንሰ ሐሳቦች ጋር ተመሳሳይ ትርጉም ከመያዙ በተጨማሪ በምድራዊም ሆነ በመንፈሳዊ ዓለም ከአደጋ ነፃ የሆነ የጤናማ ሕይወት ማረጋገጫ የሚል ከፍ ያለ ትርጉም ተሸክሟል፡፡ በግዕዝ ቋንቋም ሰላም ቀደም ሲል የተጠቀሱት ትርጉሞች እንደ ተጠበቁ ሆነው ማክበርን፣ ደስታን፣ ዋጋን የሚመለከት ትርጉም እንዳለው የሚያብራራው መድበሉ፣ ይህንን መሰል ሰላም ማግኘት የሚቻለው ራስን ከፈጣሪ ሐሳብ ጋር በማስማማት፣ ከተፈጥሮ ጋር በመታረቅና ከማኅበረሰብ አንፃርም ፍትሕና ማኅበራዊ መረጋጋት ባሰፈነ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ መኖር ሲቻል መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ሰላም ሰዎች ከራሳቸው ጋርና እርስ በርስ፣ ከፈጣሪና ከተፈጥሮ ሥርዓት ጋርም እንዲሁ ጤናማ ግንኙነት በመፍጠር በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ ሥርዓት፣ በማኅበራዊና በመንፈሳዊ ዘርፎች ውስጥ ዋስትና የሚሰጥና የሰከነ ሕይወት የሚመሩበት እንደሆነም ያሰምርበታል፡፡ ሰላም ለሰዎች ሁለንተናዊ ሕይወት ዋስትና በመስጠት ምቹ ሁኔታን ስለሚፈጥር የጽንሰ ሐሳቡ ትርጉም ሲተነተን ሰፋ ተደርጎ እንጂ በቁንፅል ሊሆን እንደማይገባም እንዲሁ፡፡ ሰላም የባህል አንዱ ክፍል መሆኑን፣ ባህልም የአንድ ሕዝብ ሁለንተናዊ መገለጫ፣ ማለትም ኅብረተሰቡ የተፈጠረበትን ማኅበረሰብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሕይወት በተገቢ ሁኔታ የማንፀባረቅ አቅሙ ከፍ ያለ እንደሆነም ያብራራል፡፡የማኅበረሰቡ ሐዘን፣ ደስታ ችግሩና ብልፅግናው የሚገልጸው በባህሉ ሲሆን፣ የዜጎች ሁለንተናዊ የግልና የማኅበራዊ ሕይወት አመራር ሥልት የሚወሰነውም በባህል አማካይነት ነው፡፡ አንድን ማኅበረሰብ ከሌላው ልዩ የሚያደርገው መታወቂያ በዋነኛነት ባህሉ ነው የሚባለውም ስለዚሁ ምክንያት መሆኑን ጥናቱ ገልጾ በማሳያነት እንግዳ ተቀባይነትን፣ ተካፍሎ በጋራ መብላትን፣ ተከባብሮና ተፈቃቅሮ መኖሩ፣ ዕድር ዕቁቡ፣ ሠርግ ሐዘኑ፣ አለባበስ አመጋገቡ ወዘተ. ስለባህል ብዙ የሚነገረውን ያህል፣ ስለሰላም ባህል እጅግም ሲነገር አይደመጥም ሲል አሳሳቢ ገጽታውን ይጠቁማል፡፡የሰላም ባህል፣ ግለሰቦች፣ ቤተሰቦች፣ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በጋራ በሚኖሩባት ኢትዮጵያ በሰላም ተከባብረው ለዘመናት እንዲኖሩ ያስቻላቸው የአኗኗር ዘይቤ መሆኑን፣ የሰላምን ቀጣይነት ከሚያረጋግጡትና ከፍተኛ ድርሻ ካላቸው የሰላማዊነት መገለጫ ባህላዊ እሴቶች መካከል ቤተሰብ ተኮር የሰላም ባህል አንዱና ቀዳሚው መሆኑንም ይገልጻል፡፡በኢትዮጵያ ለረዥም ዘመናት ጠንካራ የሰላም ባህል እንዲኖር ቤተሰብ ተኮርነት ጉልህ አስተዋጽኦ ማበርከቱን እንደሚከተለው ገልጾታል፡፡ <<የሰላም ባህላችንን ውበት ለመግለጽ የማኅበረሰባችን መሠረት የሆነውን የቤተሰብ አስተዋጽኦ ማውሳት እጅግ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን ብዙውን ጊዜ በፍቅርና በመከባበር በጋራ ሠርተን የምንኖረው፣ አደጋን የምንከላከለው፣ ሰላማዊ ሕይወት ለመምራት የምንለማመደውና መተባበርን የምንለማመደው በቤተሰብ መካከል በመኖር ነው፡፡ የአመለካከት ልዩነቶችን የምንፈታውና ለቤተሰቡ የጋራ ደኅንነትና ዕድገት ጠቃሚ መንገዶችን የመቀየስ ልምድ የምንማርበት ትልቁ ትምህርት ቤታችን ቤተሰብ ነው ቢባል ከእውነት አያርቀንም፡፡>>እንደ ጥናታዊው መድበል አገላለጽ፣ በየዘመናቱ ለሕዝቡ ሰላምና የጋራ ዕድገት ቅድሚያ እየሰጡ ያታገሉና የታገሉ ጀግኖችም አገራቸውን እንደ ቤተሰብ በመቁጠር ታላላቅ የሚሰኙ አገራዊ ቅርሶች ሊያቆዩ የቻሉት ቤተሰብ ተኮር መሠረት ላይ ታንፀው በማደጋቸው ነው፡፡በአንፃሩም በጋራ ሠርቶ በጋራ ማደግ፣ ከራስ ጥቅም ይልቅ አገርንና ሕዝብን ማስቀደም የሚሳናቸው ግለሰቦች እየተነሱ መነጋገሪያ ለመሆን የቻሉበት ሲመረመር ምክንያቱ ምናልባትም በቤተሰብ ተኮር እሴት ላይ የማደጉን አጋጣሚ ስላልተመቻቸላቸው ሊሆን እንደሚችል ለመገመት አይከብድም፡፡የብዙ ኢትዮጵያውያን ዕድገት፣ ኑሮ፣ ደስታ፣ ሐዘን፣ ወዘተ. ከቤተሰባዊ አብሮነት ጋር በእጅጉ የተሳሰረ በመሆኑ፣ በቤተሰቡ መካከል ሰላማዊ ግንኙነት እንዲቀጥል እያንዳንዱ ዜጋ ብርቱ ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ በማኅበረሰቡ ውስጥ ሥር ሰዶ የሚገኘው የቆየው የሰላም ወዳድነት ምንጭም ዜጎች ከልጅነታቸው ጀምሮ ከቤተሰቦቻቸው ከተማሯቸው ሰው አክባሪነትና በጋራ ሠርቶ የማደግ መሠረት ላይ የታነፀ እንደሆነ መረዳት አያዳግትም የሚለው ጥናቱ፣ በመሆኑም ዘላቂ ሰላም በማስፈን ቁሳዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሥነ ልቦናዊም ሆነ ማኅበራዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት በሚደረግ ጥረት ውስጥ ቤተሰባዊ ውርስ የሚኖረው ፋይዳ የላቀ መሆኑን ያሰምርበታል፡፡መሆናችንንም አትርሳ። ምንም እንኳ አባንግ ሜቶ እስካሁን ሰው ነኝ እያለ ሰው ለመሆኑ recognition ፍለጋ የሚንከራተትባት ሐገር ብትሆንም። አንድ ነን። ዛሬም ፒያሳ ያለ አባት ሴት ልጁን ለአኝዋክ ወንድ ጨክኖ የማይሰጥባት ሐገር ላይ ብንሆንም አንድ ነን። ምንም እንኳ በየአደባባዩ ኦሮሚኛ ቋንቋ የወፍ ቋንቋ ስለሆነ ለቅዳሴ አይበቃም እየተባለ የሚሰበክባት ሐገር ብትሆንም አንድ ነን። ምንም እንኳ ኦሮሞን ለደቂቃ የማትታገስ ቁስሉ ላይ ጨው የምትነሰንስ በሰበብ አስባቡ አንገቱን እንዲደፋና እንዲሳቀቅ የምትሰራ ሐገር ብትሆንም አንድ ነን። ምንም እንኳ 400 ጉምዝ በአንድ ለሊት ተገድሎ ሲቀበር ፀጥ ያለች ሐገር ብትሆንም አንድ ነን። ምንም እንኳ የኦሮሞ ጋዜጠኛን ፣ የኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቲ መሪን፣ የኦሮሞ ዘፋኝን ፣ የኦሮሞ ባለስልጣንን እየነጠለች ለማጥፋት የምትሰራ ሐገር ላይ ብንሆንም አንድ ነን። ምንም እንኳ ከአንድ ኦሮሞ ኢትዮጵያዊ ለመሆኑ ከመታወቂያው ውጪ ሌላ የባህሪ ማተማመኛ የምትጠብቅ ሐገር ብትሆንም አንድ ነን። ስለዚህ ሽሜ ምርጥ ኢትዮጵያዊ ሁን። አለበለዚያ እንደተለመደው በቅፅበት ኢትዮጵያዊነትህን ተነጥቀህ ማዳጋስካራዊ ትሆናለህ።



ማዕዘን

MAEZEN.ORG